# Inova የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ
# የቀጥተኛ ቋንቋ አጭር መግለጫ

የInova ዓላማ ለምናገለግለው በማንኛውም ማሕበረሰብ ውስጥ ላለው ማንኛው ሰው፣ ሁሉ ግዜ ደረጃውን የጠበቀ የጤና እንክብካቤ ማቅረብ ነው። በዚያም ዓላማ መሰረት፣ Inova የድንገተኛ እና ሌሎች ከሕክምና አንፃር አስፈላጊ የሆኑ የጤና አገልግሎቶችን ለግለሰቦች፣ የመክፈል አቅማቸውን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ፣ይሰጣል። ከዚህም በተጨማሪ Inovaበ Inova የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ መሠረት ለታካሚዎች የገንዘብ ድጋፍ (የበጎ ምግባር አገልግሎት) ቅናሾች ይሰጣል።

የገንዘብ ድጋፍ ቅናሾችን ለማግኘት፣ ታካሚዎች ይገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ መሙላት እና የገቢ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ እና ቨርጅንያውስጥ ስለመኖራቸው ማሳያ ሰነዶቻቸውን ማስገባት ያስፈልጋቸዋል። ቀጥሎ ያለው አንቀፅ የ Inova ን ፖሊሲ እና የገንዘብ ድጋፍ አቅርቦት ሂደቱ እንዴት እንደሚሰራ በአጭሩ ያስረዳል።[1]

## ለገንዘብ ድጋፍ ቅናሾች መስፈርቱን የሚያሟሉት አገልግልግሎቶች የትኞቹ ናቸው?

Inova በ Inova ሆስፒታሎች፣ በሌሎች የ Inova ፋኩሊዎወች እና በሀኪሞች ለታቀፉ ፋይናንሻዊ ድጋፍ እና ሌላ የህክምና አስፈላጊ የህክምና አገልግሎት ይሰጣል። የተመረጡ አገልግሎቶች (ለምሳሌ ባርያትሪክና ኮስሞቲክ ቀዶ ጥገናዎች) ሽፋን እማይሰጣቸው ሲሆን እንዲሁም በተጨማሪ በሀኪሞ የሚቀርቡ ህክምናዎች በዚህ ፖሊሲ ሽፋን ላያገኙ ይችላሉ።

እባክዎ ሙሉውን መስፈርት፤ የሚቀርቡትን ቅናሾች፣ እንዲሁም በዚህ ፖሊሲ የታቀፉ ተቋማትን እና አቅራቢዎችን ዝርዝር ለመመልከት፣ ሙሉውን የገንዘብ እገዛ ፖሊሲ በመስመር ላይ የሚከተለውን አያያዥ በመጠቀም ይመልከቱ፡ http://www.inova.org/patient-and-visitor-information/financial-help/index.jsp።

## የገንዘብ ድጋፉን መስፈርቶች የሚያሟላው ማነው?

ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ታካሚዎች፣ እንዲሁም ከተለመደው የወጣ እጅግ ከፍተኛ የሕክምና ክፍያ የሚጠየቁ ታካሚዎች ከ Inova የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍን መስፈርት ሊያሟሉ ይችላሉ። Inova መስፈርቱ መሟላቱን የሚወስነው፣ በገንዘብ ድጋፉ ማመልከቻ ውስጥ በተያያዙ ሰነዶች ላይ የተገለፀውን የታካሚውን ገቢ ከፌዴራል የድህነት መለያ መመሪያዎች ጋር በማወዳደር ነው።

---

[1] ይህ አጭር ማብራሪያ የገንዘብ ድጋፉ ፖሊሲ ሙሉ ማብራሪያ አይደለም። የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጠው በሙሉው ፖሊሲ ላይ ተመስርቶ ብቻ ነው።

በተጨማሪም Inova የኗሪነት ሁኔታ ይገመግማል። ቅናሽ ወይም አስቸኳይ አገልግሎት ለማግኘት ታካሚዎች በ ቨርጅንያ ለ30 እና ከዛ በላይ ቀናት መኖር አለባቸው።

Inova ኢንሹራንስ ላልታቀፉ፣ ገቢያቸው ከፌደራል የድህነት መመርያ አራት ዕጥፍ የሆነ እና የመኖርያ መስፈርት የሚያሟሉ ታካሚዎች 100 ፐርሰንት የፋይናንስ ድጋፍ ቅናሽ (ነጻ አገልግሎት) ይሰጣል።

Inova ከዚህ በተጨማሪ በተቀናናሾች እና የጋራ-ክፍያዎች ላይ እገዛ ለማድረግ የመድን ሽፋን ላላቸው የባለዝቅተኛ ገቢ ታካሚዎችም የገንዘብ ድጋፍ ያቀርባል። ከተለመደው በላይ እጅግ ከፍተኛ የሕክምና ክፍያ ለሚተየቁ ታካሚዎች፣ የከፍተኛ አደጋ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል።

Inova ፋይናንሳዊ ድጋፍ ከመፈቀዱ በፊት፣ ዋስትና የሌላቸው ታካሚዎች የጉዞ ጤና መርሀግብር ወይ በሌሎች ሀገራት መንግስታት ወይ ዓለማቀፍ ድርጅቶች የግለሰብ አቅርቦት የመሳሰሉ የድርጅታዊ መርሀግብር ህክምናዎች ጨምሮ ለሜዲኬር ወይ ሌሎች በመንግስት በሚደገፉ የጤና ዋስትናዎች ዓይነቶች እንዲያመለክቱ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል።

በዚህ ፖሊሲ የተሸፈኑ ማናቸውም የInova ሆስፒታሎች፣ አካሎች፣ ወይም አቅራቢዎች፣ ለገንዘብ ድጋፉ መስፈርቱን ያሟሉ ግለሰቦችን፣ የመድህን ሽፋን ያላቸው ግለሰቦች ከሚጠየቁት የሚበልጥ ክፍያ አይጠይቁም።

## ለገንዘብ ድጋፍ ማመልከት የምችለው እንዴት ነው?

ማመልከቻውን እና ስለ Inova የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ተጨማሪ መረጃ ማግነት ከፈለጉ፣ በመስመር ላይ እዚህ ይገኛል፡ http://www.inova.org/patient-and-visitor-information/financial-help/index.jsp። በተጨማሪም ወደሚከተለው አድራሻ ደብዳቤ በመላክ የገንዘብ ድጋፉን ፖሊሲ ነፃ ቅጅ መጠየቅ ይችላሉ፡

Inova Patient Financial Services
8095 Innovation Park Drive
Fairfax, VA 22031

ታካሚዎች ማመልከቻውን በመሙላት የተሞላውን ቅፅ ከሚያስፈልጉ ሰነዶች ጋር አያይዘው ከዚህ በላይ ወደተጠቀሰው አድራሻ መመለስ አለባቸው።

የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ትርጉሞች፣ ማመልከቻው እና ይህ አጭር መግለጫ በመስመር ላይ እና በጥያቄ የሚሰጡ ናቸው።

ታካሚዎች በ571-472-5880 ወደ ፋይናንሳዊ ጥራት አሰተባባሪ በመደወል በማመልከቻው ሂደት ላይ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

ታካሚዎች፣ ከዚህም በተጨማሪ የInova የታካሚ ምዝገባ ባልደረቦችን ስለ ፖሊሲው እና ስለ ማመልከቻው ሂደት መጠየቅ ይችላሉ።